# "ከአማራ ፋኖ በጎጃም" የተሰጠ መግለጫ

## (ድማማ ዲክላሬሽን)

የአማራ ሕዝብ በፋሽስቱ የብልጽግና ስርዓት በተደቀነበት የህልውና አደጋ እና ከተከፈተበት ሁሉን አቀፍ ጥቃትና ወረራ ራሱን ከመከላከል ወደ ተሟላ በትጥቅ ትግል የሚደረግ ጠላትን ማሸነፍ፣ በመላው ኢትዮጵያዊያን ፈቃድ የሚመሰረት አዲስ ስርዓት ለማዋለድ በከፍተኛ የድል ግስጋሴ ላይ መሆኑ ታዉቆ ያደረ ጉዳይ ነው። ይህንንም በከፍተኛ የእሳቤ እና ድርጅታዊ ጥንካሬ መምራት በውል እየተተገበረ እና በሚመጥን መልኩ እየተጠናከረ እየሄደ ያለ ነው።

ትግሉ አሁን ባለበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ የአምበሳውን ድርሻ እየተወጡ ያሉ የፋኖ አደረጃጀቶች የዓላማ እና የተልዕኮ ልዩነት ባይኖራቸውም አንድ ወጥ መዋቅራዊ ቅርፅ መያዝ አለመቻላቸው በትግሉ ሂደት እና ፍጥነት ላይ የፈጠረው ሳንካ በቀላሉ የሚታይ አለመሆኑን በትግሉ ሂደት ከገጠሙን ችግሮች መረዳት ችለናል።

የአማራ ሕዝባዊ ኃይል (ፋኖ) ከተመሰረተበት ዕለት ጀምሮ ባከናወናቸው ተጋድሎዎች ደማቅ ታሪክ የጻፈ ሲሆን የፋኖን እንቅስቃሴ በማስልጠን፣ በማደራጀት፣ ማስታጠቅ እና ማታገል ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል። የአማራ ሕዝብ ተጋድሎ እና የፋኖ ሠራዊት እድገት የወለደው የጎጃም እዝ ፋኖም ትግሉን ወደ ከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ረገድ ያደረገው አስተዋፅኦም በታሪክ ፊት የሚታወስ ነው።

አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እነኝህን ስሞች መጠቀም አስፈለጊ ሆኖ አለመገኘቱን እና ትግሉን በተቀናጀ የአመራር ስምሪት መምራት እና ለዚህም መግዛት የሚገባን ስለመሆኑ የህዝባዊ ኃይሉም ሆነ የእዙ አመራሮች ከተደጋጋሚ ውይይቶች በኋላ በሙሉ ድምፅ አምነንበታል። ይህንንም ስምምነትና ውሳኔ "ድማማ ዲክላሬሽን" በሚል ሰይመነዋል።

ይህንኑ የአደረጃጀት ጉዳይ እልባት ለመስጠት የተለያዩ ወገኖቻችን ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን እኛም ለሶስት ግዜያት ያህክል ፍፁም ወንድማማችነት፣ አማራዊ ጨዋነት እና ኢትዮጵያዊ ግብረ ገብነት በተላበሰ መልኩ ባደረግነው ውይይት መሰረት አንድ መዋቅር እና አመራር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ለማምጣት ተስማምተናል።

ከዚህ ውሳኔ ላይ የደረስነው ትግሉ የደረሰበት ደረጃ፣ ቀጣይ የሚጠበቅብን ከፍተኛ ኃላፊነት፣ ይህንን ትግል የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሶ ማዩት የሚፈልጉ የፋኖ ሰራዊት አባላት፣ ሌሎች አቻ

የፋኖ አደረጃጀቶች፣ በውጭ እና በሀገር ውስጥ ያሉ ደጋፊዎች ለጉዳዩ ያላቸውን ጉጉት እና ዕኑ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሁለቱም ወገን አመራሮች በአንድነት የሚመሩትን የፋኖ አደረጃጀት ማምጣት እጅጉን አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ነው።

በዚህም መሰረት "የአማራ ፋኖ በጎጃም" በሚል መጠሪያ ወደ አንድና ወጥ የፋኖ አደረጃጀት ማሳደጋችንን ለመላው የሰራዊት አመራርና አባላት፣ ለመላው የአማራ ህዝብ እና ኢትዮጵያዊያን እንዲሁም ደጋፊዎቻችን ሁሉ ስናበስር በታላቅ ደስታ ነው።

በመሆኑም "የአማራ ፋኖ በጎጃም" ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥሪዎች ያቀርባል፡-

1/ ይህ መግለጫ ከተሰጠበት እለት ጀምሮ በነባር አደረጃጀቶች ስር የሚንቀሳቀሰው የፋኖ ሰራዊት "የአማራ ፋኖ በጎጃም" አመራር እና አባል መሆኑን አውቆ በዚሁ መጠሪያ እንዲጠቀም እያሳሰብን ሚዲያዎችም ከዚህ ዕለት ጀምሮ የአማራ ሕዝባዊ ኃይል እና የጎጃም እዝ ፋኖ የሚሉትን አጠራሮች እንዳይጠቀሙ በዚህ ፋንታ "የአማራ ፋኖ በጎጃም" የሚለውን ስም ብቻ እንዲጠቀሙ እናሳስባለን።

2/ አንድ መዋቅር እና አመራር ለመፍጠር በተደረገው ውሳኔ መሰረት የአማራ ፋኖ በጎጃም አመራሮች;

1. አርበኛ ዘመነ ካሴ - ሰብሳቢ፣
2. ሻለቃ ዝናቡ ልንገረው - ም/ሰብሳቢ እና ወታደራዊ አዛዥ
    - 2.1. ሻለቃ የኔዓለም ዘለቀ - ም/ወታደራዊ አዛዥ
    - 2.2. ዘመቻ ኃላፊ - መ/አ አበበ ሰውመሆን
    - 2.3. ም/ዘመቻ ኃላፊ - መ/አ ማርቆስ አሞኘ
    - 2.4. ስልጠና ኃላፊ - ሃ/አ ታዬ ብርሐኑ
    - 2.5. ም/ስልጠና ኃላፊ - ክ/ል ጌታሁን መኮንን
    - 2.6. ሎጅስቲክስ ኃላፊ - ዘመኑ ገረመው
    - 2.7. ም/ሎጅስቲክስ ኃላፊ - መንበሩ ጌታዬ
    - 2.8. ወታደራዊ አስተዳደር - ሃ/አ ይበልጣል መልካሙ
3. አርበኛ እና ጠበቃ አስረስ ማረ ዳምጤ - ም/ሰብሳቢ እና የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ
    - 3.1. ግሩም ምሳሌ - ም/የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ
4. የውጭ ግንኙነት እና የዲያስፖራ ጉዳዮች መምሪያ -

4.1. ስሜነህ ሙላቱ - ኃላፊ

4.2. ኃ/ሚካኤል ባዬ - ም/ኃላፊ

5. የቀጠናዊ ትስስር መምሪያ -

5.1. የቆዬ ሞላ - ኃላፊ

5.2. አዲሱ ፈጠነ - ም/ኃላፊ

6. የህዝብ ግንኙነት መምሪያ

6.1. ማርሸት ፀሐው - ኃላፊ

6.2. ዮሐንስ አለማየሁ - ም/ኃላፊ

7. ስትራቴጂክ ጉዳዮች መምሪያ

7.1. ተሰማ ካሳሁን - ኃላፊ

7.2. ጎበዜ ጌታሁን - ም/ኃላፊ

8. የፋይናንስ እና ንብረት አስተዳድር መምሪያ

8.1. ማንችሎት እሱባለው - ኃላፊ

8.2. ዳኛው ሽባባው - ም/ኃላፊ

9. የጽ/ቤት ኃላፊ

9.1. ይትባረክ አንዳርጌ - ኃላፊ

9.2. በለጠ አብርሐም - ም/ኃላፊ

10. የአደረጃጀት ዘርፍ መምሪያ

10.1. እሸቱ ጌትነት - ኃላፊ

10.2. ስለሺ ከበደ - ም/ኃላፊ

11. መረጃ እና ደህንነት መምሪያ - XXX

ሆነው እንዲመሩ ተስማምተናል።

3/ ይህ መግለጫ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ የሚሰበሰብ የሎጅስቲክስ እና የፋይናንስ ድጋፍ "የአማራ ፋኖ በጎጃም" በሚሰጠው መመሪያ እና ለዚሁ ጉዳይ በሚያደራጀው መምሪያ (የስራ ክፍሎች) መሰረት እንዲፈፀም እና በዚህ አግባብ እንዲከናወን መወሰናችንን እናስታውቃለን። ሁሉም መዋቅራዊ ጉዳይ በተመሳሳይ አካሄድ የሚፈፀም ይሆናል።

4/ ለመላው የአማራ ህዝብ እና ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በዚህ ውሳኔያችን መሰረት ኃይላችንን በማጠናከር ለምንፈጽመው ከፍተኛ ጠላትን የማሽመድመድ እና ወደ ድል የመገስገስ ሂደት

በሙሉ ልብ እና ቀና ፍላጎት ከጎናችን በመሰለፍ ይህንን ሀገር እና ህዝብ ጠል ጥገኛ ፋሽስት ስርዓት በማስወገድ ለፍትሕ እና እኩልነት የቆመ አዲስ ኢትዮጵያዊ ስርዓት ለመመስረት ዝግጁ እንድትሆኑ ብርቱ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

5/ በሌሎች የአማራ ክፍለ ግዛቶች እና ቀጠናዎች ያላችሁ የፋኖ አደረጃጀቶች እንደ አንድ አማራ ልንሰራ ያቀድነውን እና እየደከምንበት ያለውን አንድ ወጥ ደርጅት ለመፍጠር ለምናደረገው ርብርብ እና ወንድማዊ ጥሪ ራሳችሁን እንድታዘጋጁ እና በፍጥነት የጋራ ቤታችንን እንድንቀልስ ጥሪ እናቀርባለን። ይህም የትግላችን ወሳኙ ምዕራፍ ነው።

6/ ለትግሉ አበርክቶ ያለው የተለያየ አቅም፣ ሙያ እና ፍላጎት ያላችሁ ምሁራን ያለንበትን የህልውና ትግል መቀላቀል ታሪካዊ የውዴታ ግዴታችሁ መሆኑን ተገንዝባችሁ እና ድርጅታችን አቅም እና ፍላጎቱ ያለውን ሁሉ የሚያስተናግድበት መደላድል እንዳለም አውቃችሁ ትግሉን እንድተቀላቀሉ እናሳስባለን።

7/ በመጨረሻም ትግላችን የደረሰበትን ደረጃ በውል መገንዘብ እንደሚገባ እየገለጽን ይህ አደረጃጀት የምንታገልለትን ህዝብ፣ የትግሉን ደጋፊዎች፣ የሰራዊታችንን ወቅታዊ ፍላጎት በአጠቃላይ ጊዜው የጠየቀውን የመዋቅርና አመራር ማጠናከር ታሳቢ አድርገን በቅንነት ያዋለድነው አደረጃጀት መሆኑን የሚመለከተው ሁሉ እንዲረዳው እና ከጎናችን እንዲቆም ጥሪ እናቀርባለን።

አዲስ ትውልድ! አዲስ አስተሳሰብ! አዲስ ተስፋ!

ድል ለአማራ ሕዝብ!

የካቲት 15/2016 ዓ.ም

ግሽ ዓባይ - ጎጃም፣ ኢትዮጵያ